**የሕመም ፈቃድ እና ኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ጥያቄዎች፡፡**

1. **የ መንግሥት ባለ ሥልጣናት የሥራ ቦታቸውን ከ ኮቪ-19 ጋር በ ተያያዘ ጉዳዮች የሚዘጉ ከሆነ ሠራተኞች የሚከፈልበት የሕመም ፈቃድ መጠቀም ይችላሉ? አሠሪው ሥራውን በተገቢወ ሁኔታ እየሠራ ቢሆንና ፣ ነገር ግን በ አገሪቱ አስተዳደር ትእዛዝ ምክንያት የሥራዎች ላይ ገደቦች ቢኖሩስ?**
   በ ቅጥር ላይ ያሉ ሰራተኞች የ ተጠራቀመ የሕመም ፈቃድ መጠቀም ይችላሉ። አሠሪው አንድ ን ሠራተኛ ከ ሥራው ካባረረ ፣ ተቀጣሪው ለሥራ እጥነት ክፍያ ማመልከት ይችላል ፡፡
2. **ሠራተኞች አሁንም ተቀጣሪ መሆናቸውን እንዴት ያውቃሉ?**
   አሠሪዎች አንድን ሠራተኛ ካሰናበቱት፡ እንዳሰናበቱት ማሳወቅ ግዴታ አለባቸው ፡፡ ሰራተኞች ከስራ ውጭ ከሆኑ ወይም የስራ ሰዓታቸው ከቀነሰ ሰራተኞች ለስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች ማቅረብ ይችላሉ ፡፡
3. **ትምህርት ቤት ወይም የሰራተኛ ልጆች ማረፊያ ቦታ በጤና ስጋት ለጊዜው ከተዘጋ ፣ ሠራተኞች ልጆቻቸውን ለመንከባከብ የተጠራቀመ የህመም ፈቃድ መጠቀም ይችላሉ?**
   አዎ
4. **የሰራተኛው የሥራ ቦታ ወይም የልጁ ትምህርት ቤት ወይም የእንክብካቤ መስጫ ቦታ የሚዘጋ ከሆነ አሠሪው የሰራተኛውን የህመም ፍቃድ ጥያቄን ወይም ሠራተኛው ከቤት ሆኖ የመስራት ጥያቄን ሊከለክል ይችላል?**
   አይደለም
5. **አሠሪው በኮቪድ-19 የመጋለጥ አደጋን ለመቀነስ በጊዜያዊነት የንግድ ቦታውን ለመዝጋት ከፈለገ ፤አንድ ሠራተኛ ይህን ክፍተት ለመሸፈን የህመም ፈቃድ ከክፍያ ጋር መጠቀም ይችላልን?**
   አሰሪው ኮቪድ-19ን ለመከላከል የንግዱ ቦታውን ለጊዜው ለመዝጋት ከወሰነ አሠሪው ለሰራተኛው የህመም ፈቃድ ከክፍያ ጋር የመስጠት ግዴታ የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ አሠሪው በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሕመም ፈቃድ ከክፍያ ጋር መጠቀምን ሊፈቅድ ይችላል ፡፡
6. **አሠሪዎች የሰራተኞቻቸውን በ ኮቪድ-19 የመጋለጥ ፍራቻን ምክንያት በማድረግ ሠራተኞችን ከሥራ እንዲወጡ ማድረግ ይችላሉ?**
   አንድ አሠሪ ተቀጣሪ ሠራተኞችን ከሥራ እንዲባረሩ ሊያደርግ ይችላል:: ይሁን እንጂ አሰሪው ሰራተኛው **በስራ ገበታው ያልተገኘባቸውን** ጊዜያት ለማካካስ ፤ ሰራተኛውን የህመም ፈቃዱ ከ ክፍያ ጋር እንዲጠቀም ሊያስገድደው አይችልም።
7. **አንድ ሠራተኛ በኮቪድ-19 ጥርጣሬ ምክንያት ሥራው ላይ መቀጠል ባይችል፤ ተጠራቀመ የሕመም ፈቃድ ከ ክፍያ ጋር መጠቀም ይችላል?**
   አንድ ሠራተኛ የ ተጠራቀመ የሕመም ፈቃድ መጠቀም ይችላል ፡፡ ይሁን እንጂ አሰሪው ሰራተኛው በስራ ገበታው ያልተገኘባቸውን ጊዜያት ለማካካስ ፤ ሰራተኛውን የ ተጠራቀመ የህመም ፈቃዱን እንዲጠቀም ሊያስገድደው አይችልም።
8. **አንድ ሠራተኛ ከ ታመመ ወይም ከ ኮቪድ-19 ጋር የሚዛመዱ ምልክቶች ካሳየ የ ተከማቸ የሕመም እረፍት ከ ክፍያ ጋር መጠቀም ይችላል?**
   ሰራተኞች የ አካል ጉዳቶች ፣ በሽታዎች ወይም ሌላ የጤና እክል ካለባቸው የ ተጠራቀመ የሕመም ፈቃድ መጠቀም ይችላሉ ፡፡ የ አካል ጉዳቶች ፣ በሽታዎች ወይም ሌላ የጤና እክል ያለባቸው የ ቤተሰብ አባላትን ለመንከባከብ የ ተጠራቀመ የሕመም ፈቃድ መጠቀም ይችላሉ ፡፡
9. **አንድ የ ህክምና ባለሙያ ሠራተኛው የኮቪድ-19 ምልክቶች ካሳየ ወይም ተጋላጭ መሆኑን ቢያሳውቅ፤ ሰራተኛው የ ተጠራቀመ የሕመም እረፍት ከ ክፍያ ጋር መጠቀም ይችላል?**
   አዎ
10. **ከ ኮቪድ-19 ጋር ለሚዛመዱ ህመሞች ወይም ምልክቶች ታማሚው የ ህክምና ምርመራ ፣ እንክብካቤ ፣ ህክምና ፣ ወይም የ መከላከያ ህክምናን የሚሹ ከሆነ የተጠራቀመ የህመም ፈቃድ ከ ክፍያ ጋር መጠቀም ይችላሉ?**
    አዎ

**11. አሠሪ ለ ሕመም እረፍት ከ ክፍያ ጋር ክፍያ ጊዜ (PTO) መርህ ግብር አንድ ሲጠቀም፤ ከ ከኮቪድ-19 ጋር በ ተያያዘ ሰራተኛው የ PTO ፈቃድ ን መጠቀም ይችላል?**
አዎ

**12. አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው ተጨማሪ የሚከፈላቸውን የሕመም እረፍት ሊያወጡ ወይም በ ኮቪድ-19 ምክንያት የሚመጣው የደሞዝ አለመከፈል እንዴት ሊሸፍኑ ይችላሉ?**

- አሠሪዎች ከሚከፍሉት የሕመም ፈቃድ ሕጎች ከሚፈቅድው በተጨማሪ የበለጠ ጭማሪ ክፍያ ሊሰጡ ይችላሉ ፡፡
- አሠሪዎች ከዝቅተኛ ፈቃድ ካላቸው ዓላማዎች በላይ ለተጨማሪ ዓላማዎች ተጨማሪ ክፍያዎችን እንዲጠቀሙ አሠሪዎች ሊፈቅዱላቸው ይችላሉ ፡፡
- አሠሪዎች ከ ኮቪድ-19 ጋር በ ተያያዘ የሚከፈለውን የህመመ ፈቃድ የሚጠቀሙ ሰራተኞች ለጊዜው የማረጋገጫ መስፈርቶችን ማስቀመጥ ይችላሉ ፡፡
- አሠሪዎች የሕመም ፈቃድ ከ ክፍያ ጋር አዳዲስ ፖሊሲዎችን ሊያወጡ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ ፡፡
- አሠሪዎች የ ቅድመ ክፍያ ሊፈጽሙ ይችላሉ ይህ የሚሆነው ግን አስፈላጊው የ ዳግም ቅነሳ ህጎች እስከተሟሉ ድረስ ነው፡፡
- አሠሪዎች የጋራ ፈቃድ የመጠቀምን ፖሊሲዎች ሊተገብሩ ይችላሉ ፡፡ የ ተጠራቀመ የ አመት እረፍት ያላቸው ሰራተኞች ለሥራ ባልደረቦችቸው በ ፈቃደኛነት ማስተላለፍ ይችላሉ ፡፡